## ምዕራፍ ፲፰

## ዘዓርብ ስቅለት ዘሰርከ ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር አዶናይ፡ዘበትርጓሜሁ እግዚእ ኤልሻዳይ፡በከርሠ ደመና ዘየዐቍር ለማይ፡ ዘያዐርጎ እምቀላይ፡ ዘይረብቦ በገጸ ሰማይ፡ወይገለብቦ ለብ ርሂን ፀሐይ፡ ዘያስተባሪ አክራመ በሐጋይ ወመፀወ በፀደይ፡ ከንተርሳቲሆሙ ዘገብረ በዘይትዔረይ፡ለቀዳሚ ምስለ ካልአይ ወሣልሳዊ ምስለ ራብዓይ፡ ፍልጠተ ዓመታት በዘይትሌለይ፡ውስተ ልበ መሐስባን በዘይትኄለይ፡ሎቱ ስብሐት ለብሑተ ሥልጣን ወዕበይ፡ለዓለመ ዓለም አሜን፡ ወአሜን፡፡

፪ ንንግርኬ ዘለፋሁ ለመንክዮስ ዘይቤ ምትሐት ሥጋሁ ለክርስቶስ ወአኮ ሥጋ እጓለ እመሕያው፡፡ አንከር አበደከ አ መንክዮሰ እፎ አፍቀርኮ ከመ ትሰምዮ ምትሐተ እምትስምዮ ሥግወ ዘእም ወለተ አዳም ወሔዋን፡፡ሶበሰ ኢሥግው ውእቱ እምዕብራዊት ወለተ ዕብራውያን ኢውሉድ ውእቱ እምኔሃ፡፡ወእመሂ ኢውሉድ ውእቱ እምኔሃ ኢሐፁን ውእቱ በሐሊበ አጥባቲሃ፡፡ወእመሂ ኢሐፁን በሐሊበ አጥባቲሃ ኢሐቴፍ ውእቱ በአብራኪሃ፡፡ ወእመሂ ኢሐቴፍ በአብራኪሃ ኢልኩፍ ውእቱ በአጻብዒሃ ዘይቤ በእንቲአሁ ማቴዎስ ወንጌላዊ ውእቱ በከመ ሥርዓተ ሕዝባ፡፡ወእመሂ ኢከሱብ ውእቱ በከመ ሥርዓተ ሕዝባ ኢጥሙቅ ውእቱ በፈለገ ዮርዳኖስ እንዘ ይትገሰስ ርእሶ በኀበ ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ፡፡ወእመሂ ኢጥሙቅ በፈለገ ዮርዳኖስ ኢቅንው ውእቱ በሐጻውንተ መስቀል፡ ወእመሂ ኢቅንው በሐጻውንተ መስቀል ኢቅቱል ውእቱ በእንተ ቤዛ ብዙኃን ወእመሂ ኢቅቱል ውእቱ በእንተ ቤዛ ብዙኃን ኢድኅነ አንተ መንክዮስ በሞተ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

፫ ዘበእንቲአሁ ይቤ እግዚአብሔር በመጽሐፈ ኦሪት አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ ምትሐትን፡፡ወካዕበ ዘበእንቲአሁ ተብህለ በመዝሙር መሐለ እግዚአብሔር ለዳዊት በጽድቅ ወኢይኔስሕ እስመ እም ፍሬ ከርሥከ እነብር ዲበ መንበርከ ምትሐትን፡፡ዘበእንቲአሁ ተብህለ በአፈ ኢሳይያስ ትወፅእ በትር

## ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

## የዓርብ ስቅለት የሰርክ ምንባብ

፩ ትርጉሙ ጌታ ኤልሻዳይ ማለት በሆነ አዶናይ እግዚአብሔር ስም ውኃን በደመና ማኅፀን የሚቋጥረው ከውቅያኖስ የሚያወጣው በሰማይም ላይ የሚዘረጋው የፀሐይን ብርሃን የሚሸፍነው ክረምትን በበጋ መፀውንም በፀደይ የሚያፈራርቅ ለፊተኛው ከሁለተኛው ጋር ለሦስተኛውም ከአራተኛው ጋር የዘመናት መለየት በሚለይ ገንዘብ የዘመን ክፍለ ጊዜያቸውን በማስተካከል የሠራ በባልቴቶች ልብ በሚታሰብ ገንዘብ የሥልጣንና ጌትነት ባለቤት ለሆነ ለእርሱ ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን አሜን፡፡

፪ የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው የሰው ልጅ ሥጋም አይደለም ያለ የመንክዮስን ተግሣጽ እንናገር፡ መንክዮስ ሆይ ሰንፍናህን አደንቃለሁ ከአዳምና ከሔዋን ሴት ልጅ ሰው ሆኖ የተወለደ ከምትለው ይልቅ ምትሐት ትለው ዘንድ ምንኛ ወደድኸው፡ ዕብራዊት ከሆነች የዕብራውያን ሴት ልጅ ሰው የሆነ ባይሆንስ ከእርሷ ያልተወለደ ነው ከእርሷም ካልተወለደ በጡቶቿ ወተት ያደገም አይደለም በጡቶቿም ወተት ያደገ ካልሆነ በጉልበቶቿ ያልታቀፈ ነው፡ በጣቶቿ አልተነካም እንደ ወገኖቿም ሥርዓት አልተገረዘም በወገኖቿም ሥርዓት ያልተገረዘ ከሆነ ራሱን በዘካርያስ ልጅ በዮሐንስ እጅ ተዳስሶ በዮርዳኖስ ወንዝ የተጠመቀ አይደለም፡ በዮርዳኖስም ወንዝ የተጠመቀ ካልሆነ በመስቀል ችንካሮች የተቸነከረ አይደለም፡፡ በመስቀል ችንካሮች ካልተቸነከረም ለብዙዎች ቤዛ የተገደለ አይደለም ስለ ብዙዎች ቤዛም የተገደለ ካልሆነ አንተ መንክዮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አልዳንህም፡፡

፫ እግዚአብሔር ስለርሱ በኦሪት መጽሐፍ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ብሎ የተናገረለት ምትሐት ነውን፡፡ ዳግመኛም ስለርሱ በመዝሙር እግዚአብሔር ከባሕርይህ የተከፈለ ልጅህን በዙፋንህ አስቀምጣለሁ ብሎ ለዳዊት በእውነትማለ አይጸጸትምም ተብሎ የተነገረለት ምትሐት ነውን፡፡ በኢሳይያስ አንደበት ስለርሱ

እምሥርወ ዕሤይ ወየዐርግ ጽጌ እምኵንዱ ምትሐትኑ፡፡ ዘፍ፫÷፳፪ መዝ፻፴፩÷፲፩ ኢሳ፲፩÷፩

፭ ወካዕበ ተብህለ በእንቲአሁ ናሁ ይሌቡ ቍልዔየ ይትሌዓል ወይከብር ወያንክሩ አሕዛብ በእንቲአሁ ምትሐትኑ፡ወዓዲ ተብህለ በእንቲአሁ አነ አበቍል ቀርነ ለዳዊት ወአስተዴሉ ማኅቶተ ለመሲሕየ ምትሐትኑ፡፡ ወዘ በእንቲአሁ ተብህለ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወወሊዳ ትሰምዮ አማኑኤል ምትሐትኑ፡፡ወዓዲ መጽሐፈ ልደቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም ምትሐትኑ፡፡ወካዕበሙ ይቤ ዮሐንስ ወንጌላዊ ዘበእንቲአሁ ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ ምትሐትኑ፡፡ወዓዲ ዘበእንቲአሁ ይቤ ጳውሎስ እምዘርአ ዳዊት ዘመጽአ በሥጋ ሰብእ ምትሐ ትኑ፡፡መዝ፻፴፩÷፲፯ ኢሳ፯÷፲፬ ማቴ፩÷፳ ዮሐ፩÷፲፬

፮ ወዓዲ ዘይቤ ለሊሁ ወዓዲ ትፈቅዱ ትቅትሉኒ ብእሴ ዘጽድቀ እነግረከሙ ምትሐትኑ፡፡ወካዕበሙ ዘይቤ እስመ ወልደ እግዚአብሔር ወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ ምትሐትኑ፡፡ወዘይቤ አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ዘበልዐ ሥጋየ የሐዩ በእንቲአየ ወዘሰትየ ደምየ ኢይጥዕሞ ለሞት ምትሐትኑ፡፡ወዘይቤ ካዕበ እስመ ሥጋየኒ መብልዕ ጽድቅ ዘበአማን ወደምየኒ ስቴ ሕይወት ዘበአማን ምትሐትኑ፡፡ወዘይቤ ዓዲ እመ ኢበላዕክሙ ሥጋሁ ለወልደ እጓለ እመሕያው ወኢሰተይክሙ ደሞ አልብክሙ ሕይወት ዘለዓለም ምትሐትኑ፡ወዘይቤ ካዕበሙ ዝ ኅብስት ዘኢሁበክሙ አነ ሥጋየ ውእቱ ወዝኒ ጽዋዕ ዘኢሁበክሙ ደምየ ውእቱ. ምትሐትኑ፡፡ ወዘይቤ ዓዲ በከመ አብ ሕያው ወአነሂ ሕያው ወአነሂ ሕያው በእንተ አብ ወዘበልዐ ሥጋየ የሐዩ በእንቲአየ ምትሐትኑ፡፡ወዘይቤ ካዕበን ሥትዎ ለዝንቱ ቤተመቅደስ ወበሠሉስ መዋዕል አነሥኦ፡፡ወውእቱሰ በእንተ ቤተ ሥጋሁ ይቤሎሙ ምትሐትኑ፡፡ወዘይቤ ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ኅብስት ሥጋየ ለዘበእንቲአከሙ ይትፌተት ወይትወሀብ ለቤዛ ብዙኃን ምትሐ ትኑ፡፡ወዘይቤ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ዘሐዲስ ሥርዓት ምትሐትኑ፡፡ወዘይቤ አባ አኅልፋ እምኔየ ለዛቲ ጽዋዕ ወአመኮሰ ፈቃደ ዚአከ ለይኩን ምትሐትኑ፡፡ወዘይቤ እስመ መንፈስ ይፈቱ ወሥጋ ይደክም ምትሐትኑ፡፡ ማቴ፳፮÷፳፮ ዮሐ፮÷፲፬ ፤፮÷፶፫

ከዕሤይ ሥር በትር ትወጣለች ከግንዱም አበባ ይወጣል የተባለለት ምትሐት ነውን፡፡
ዘፍ፫÷፳፪ መዝ፻፴፩÷፲፩ ኢሳ፲፩÷፩

፭ ዳግመኛም ስለርሱ እኔ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ ለመሢዬም መብራትን አዘጋጃለሁ ተባለ፡ ስለርሱም እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ወልዳም ስሙን አማኑኤል ትለዋለች ተብሎ የተነገረ ምትሐት ነውን፡፡ ከእንደገናም ወንጌላዊ ማቴዎስ ስለርሱ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ መጽሐፍ ያለ እርሱ ምትሐት ነውን፡፡ ሁለተኛም ወንጌላዊ ዮሐንስ ስለርሱ ያም ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም ላይ አደረ ያለ እርሱ ምትሐት ነውን፡፡ ጳውሎስም ስለርሱ ከዳዊት ዘር በሰው ሥጋ ይመጣል ያለ ምትሐት ነውን፡፡ መዝ፻፴፩÷፲፯ ኢሳ፯÷፲፬ ማቴ፩÷፳ ዮሐ፩÷፲፬

፮ ሁለተኛም እርሱ ባለቤቱ ዳግመኛም እውነት የምነግራችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትሻላችሁ. ብሎ የተናገረ እርሱ ምትሐት ነውን፡ ሁለተኛም የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነውና ያለ እርሱ ምትሐት ነውን፡ እኔ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ ነኝ ሥጋዬን የበላ በእኔ ምክንያት በሕይወት ይኖራል ደሜንም የጠጣ ሞትን አይቀምሰውም ያለ ምትሐት ነውን፡ ሁለተኛም ሥጋዬ እውነተኛ የጽድቅ መብል ነው ደሜም እውነተኛ የሕይወት መጠጥ ነው ያለ እርሱ ምትሐት ነውን፡ ከእንደገናም የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ የዘላለም ሕይወት የላችሁም ያለ ምትሐት ነውን ሁለተኛም አብ ሕያው እንደ ሆነ እኔም የአብ ልጅ ስለሆንሁ ሕያው ነኝ፡ ሥጋዬን የበላ የእኔን ሥጋ ስለበላ በሕይወት ይኖራል ያለ ምትሐት ነውን ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም እነሣዋለሁ ያለ እርሱ ግን ስለ ሥጋው ቤት ይላቸው ነበር እርሱ ምትሐት ነውን፡ ይህ ኅብስት ስለ እናንተ የሚቆረስ ለብዙዎችም ቤዛ ሆኖ የሚሰጥ ሥጋዬ ነው እንካችሁ ብሉ ያለ ምትሐት ነውን፡ ይህ ጽዋ የአዲስ ሥርዓት ደሜ ነው እንካችሁ ጠጡ ያለ ምትሐት ነውን አባት ሆይ ይህችን ጽዋ ከእኔ አርቃት ካልሆነ ግን የአንተ ፈቃድ ይሁን ያለ እርሱ ምትሐት ነውን፡ መንፈስ ይበረታልና ሥጋ ግን ይደክማል ያለ ምትሐት ነውን፡፡
ማቴ፳፮÷፳፮ ዮሐ፮÷፲፬ ፤፮÷፶፫

www.ethiopianorthodox.org

፯ ዘበብስራተ ገብርኤል ተሠገወ እምን ጽሕት ድንግል እንተ ኢተአምር ብእሴ በሀገ ረ ገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት ምትሐትኑ፡፡ ዘበ ቤተልሔም ተወልደ ወበእደ ሰሎሚ ተገሰ ምትሐትኑ፡ዘበአጽርቅት ተጠብለለ ወዲበ ምጽ ንጋዕ አስመከ ምትሐትኑ፡፡በከመ ሥርዓተ ሕፃናት ዘአብቀወ ለጠቢወ ጥብ ወአመ ሰሙ ን ዘወሰ ድዎ ለተከስቦ ምትሐትኑ፡፡ ዘልህቀ በበን ስቲት እንዘ ይትሌተት ልባኑ በሥርዓተ ደቂቅ ወአመ ልህቀ ዘከሠተ አፋሁ በነገረ ዕብራይስጢ በከመ ነገደ ሕዝባ ለእሙ ምት ሐትኑ፡፡ ሉቃ፩፥፳፯፡፪፥፲፪፡፳፩

፰ ዘበልዐ ምስለ ኃጥአን ወረፈቀ ምስለ ጸብሐን ምትሐትኑ፡፡ዘአኀዘ እዴሃ ለወ ለተ ኢያኢሮስ ወይቤላ ተንሥኢ ጣቢታ ወዘ ገሰሰ ንፍቆ ለወልደ መበለት ወአንሥኦ ሕያ ዎ ምትሐትኑ፡፡ዘተፍአ ውስተ እዘኒሁ ለጽሙ ም ወይቤሎ ኤፍታሕ ተፈታሕ ተረኃው ብሂ ል ምትሐትኑ፡፡ ወኀፅበ በቀቢዐ ምራቁ ዘምስለ ጽቡር ዘፈጠረ ሎቱ አዕይንተ ለጤሜዎስ ወልደ በርጤሜዎስ እንዘ ቀዲሙ ኢተፈጥረ ሎቱ አዕይንት ምትሐትኑ፡፡ዘኀፀበት እገሪሁ ዘማ በአንብዓ ወዘአኮሰት ዕፍረተ ዘቢረሌ ወሦጠት ዲበ ርእሱ እኅተ አልዓዛር ምትሐ ትኑ፡፡ዘበከየ በእንተ አልዓዛር ወይቤ አይቴ ቀበርክምዎ ወእምዝ ጸውዖ ወአንሥኦ ሕያወ ከመ ዘኢሞተ ምትሐትኑ፡፡ ማቴ፱፥፳፭ ዮሐ፱፥፯ ፡፲፩፥፴፫፡፲፪፥፫

፱ ዘርኅበ ወጸምአ ከመ ነዳይ ወደከመ ወሃፈወ በአምጣነ ብእሲ ምትሐትኑ፡፡ዘተአ ኀዘ እምእግብርተ ሊቀ ካህናት ወዘሐመይዎ እደዊሁ ከመ ሠራቂ ምትሐትኑ፡፡ዘተጸፍዐ መ ላትሒሁ በዓውደ ሰቃልያን ወተኰርዐ ርእሰ በበትረ ሕለት ምትሐትኑ፡፡ዘተቀሥፈ በጥብ ጣቤ መኰንን ወዘተቀጸለ አክሊለ ሦክ ምት ሐትኑ፡፡ዘነሥእዎ ሰገራተ ሰጺራ ወወሰድዎ መካነ ቀራንዮ እንዘ ይጸውር መስቀሎ ምትሐ ትኑ፡፡ዘተሰቀኖረ እደዊሁ ወእገሪሁ በቅንዋተ ኃጺን ወተለከወ ውስተ ጕንደ መስቀል ምትሐ ትኑ፡፡ ዘመጠወ ነፍሶ ኀበ አቡሁ ወይቤ አባ ውስተ እዴከ አማኅጽን ነፍስየ ምትሐትኑ፡፡ ዘሦጣ ለነፍሱ ውስተ ሥጋሁ ወተንሥአ በኃይለ ለ መለኮቱ ምትሐትኑ፡፡ ይክል ገቢረ ዘንተ ኩሎ፡፡

፲ ኢአከለከኑ አ አብድ ዘቀሠምነ ለከ ሰምዐ እመጻሕፍተ ነቢያት ወሐዋር ያት፡፡ ወእመሂ ትፈቅድ ለከ ተውሳከ ብየ

፯ በገብርኤል የምሥራች ቃል ወንድ ከማታውቅ ከንጽህት ድንግል ናዝሬት በምትባል በገሊላ ሀገር በሥጋ የተወለደ እርሱ ምትሐት ነውን፡፡ በቤተልሔም የተወለደ በሰ ሎሜም እጅ የተዳሰሰ እርሱ ምትሐት ነውን፡፡ በጨርቅ የተጠቀለለ በግርግምም የተኛ ምትሐት ነውን፡፡ እንደ ሕፃናት ሥርዓት ጡት ለመጥባት አፉን የከፈተ በስምንት ቀንም ለመገረዝ የወሰዱት ምትሐት ነውን በሕፃናት ሥርዓት እንደበቱ እየተኮላተፈ በየጥቂቱ ያደገባደገም ጊዜ እንደ እናቱ ወገኖች አፉን በዕብራይስጥ ቋንቋ የፈታ ምትሐት ነውን፡፡
ሉቃ፩፥፳፯፡፪፥፲፪፡፳፩

፰ ከኃጥአን ጋር የተመገበ ከቀራጮችም ጋር የተቀመጠ ምትሐት ነውን የኢያኢሮስን ሴት ልጅ እጇን ይዞ ጣቢታ ተነሺ ያላት የመበለቲቱንም ልጅ አካሉን ዳስሶ በሕይወት ያስነሣው እርሱ ምትሐት ነውን፡፡ በደንቆሮ ጆሮ እንትፍ ብሎ ተፈታ ተከፈት ሲል ኤፍታኅ ያለ እርሱ ምትሐት ነውን፡ ሁለተኛም ምራቁን በጭቃ ለውሶ ቀድሞ ዓይን ያል ተፈጠረለት ሲሆን ለበርጤሜዎስ ልጅ ለጤ ሜዎስ ዓይንን የፈጠረለት ምትሐት ነውን፡፡ አመንዝራይቱ ሴት እግሮቹን በዕንባዋ ያጠበችው የአልዓዛርም እኅት የብልቃጡን ሽቱ በራሱ ላይ ያፈሰሰች እርሱ ምትሐት ነውን ወዴት ቀበራችሁት ብሎ ስለ አልዓዛር ያለቀሰ ከዚያ በኋላ ጠርቶ እንዳልሞተ ሰው በሕይወት ያስነሣው ምትሐት ነውን፡፡
ማቴ፱፥፳፭ ዮሐ፱፥፯፡፲፩፥፴፫፡፲፪፥፫

፱ እንደ ደሀ የተራበና የተጠማ እንደ ሰውም የደከመ የወዛ እርሱ ምትሐት ነውን፡ በሊቀካህናት ባለሟሎች የተያዘ እጆቹንም እንደሌባ ያሠሩት እርሱ ምትሐት ነውን በሰቃዮች አደባባይ ጉንጮቹ በጥፊ የተመታ ራሱም በዘንግ የተመታ ምትሐት ነውን፡፡ በዳኛ መግረፊያ የተገረፈ የእሾህ አክሊልንም የተቀዳጀ እርሱ ምትሐት ነውን፡ ጭፍሮች የያዙት መስቀሉንም ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ የወሰዱት ምትሐት ነውን እጆቹንና እግሮቹን በብረት ችንካሮች የተወጋ በመስቀሉም ግንድ የተቸ ነከረው ምትሐት ነውን፡ አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ ብሎ ነፍሱን ለአባቱ የሰጠ ምትሐት ነውን፡ ነፍሱን ወደ ሥጋው የመለሳት በመለኮቱም ኃይል የተነሣ ምትሐት ነውን፡ ይህን ሁሉ ማድረግ ይቻለዋል፡፡ ማቴ፩፥፫
ሉቃ፳፪፥፶፬ ፡፳፫፥፶፯

፲ አንተ ሰነፍ ከነቢያትና ከሐዋርያት መጻሕፍት መርጠን ያቀረብንልህ ማስረጃ አልበቃምን፡ ተጨማሪም ከፈለግህ ወንጌላዊ

www.ethiopianorthodox.org

ስምዓ ጽድቅ ዘይቤ ወንጌላዊ ማቴዎስ፡፡ ወሶበ ይከውን ራብዕት ሰዓት ሌሊት መጽአ ኀቤሆሙ እንዘ የሐውር ዲበ ባሕር፡፡ወሶበ ርእይዎ አርዳኢሁ እንዘ ዲበ ባሕር የሐውር ደንገፁ ወተሀውኩ እንዘ ይብሉ ምትሐት ውእቱ ወመሰሎሙ መንፈስ ዘአስተርአዮሙ፡፡ ወእምፍርሀተ ግርማሁ አውየዉ፡፡ወበጊዜሃ ተናገሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ሶቤሃ እንዘ ይብል ተአመኑ ወኢትፍርሁ አነ ውእቱ፡፡ ማቴ፲፬፥፳፫-፳፯

፲፭ ሰበሰቤ ምትሐት ውእቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ እምኢይቤ ወንጌላዊ ወመሰሎሙ ጋኔን ዘአስተርአዮሙ፡፡ወበእንተ ሥጋዌ ፍጽምት እንተ ለብሰ ወልደ እግዚአብሔር ይቤ መሰሎሙ ምትሐት ዘአስተርአዮሙ፡፡በእንተ ምንትኑ ዘመሰሎሙ ምትሐት፡እስመ ግርማ ሌሊት መፍርህ ወኪዶተ ሞገደ አብሕርትኑ ኢብውሐ ሎቱ ለወልደ እጓለ እመሕያው፡፡ ወሶበ ርእዩ ሥጋ ዘያንሶሱ ዲበ ማይ ፈርሁ እስመ ኢያአመኑ ከመ እግዚእ ኢየሱስ ውእቱ፡፡ወሶበ ይቤሎሙ አነ ውእቱ አእመሩ ወኢፈርሁ፡፡እስመ ምትሐት ብሂል አስተርእዮ መናፍስት በዘኢዘአሆሙ አርአያ፡፡ያስተርእዩ በአምሳለ ዘሥጋ እንዘ አልቦሙ ሥጋ፡ ምዕረ ያስተርእዩ ወምዕረ ይሤወሩ ወአስተርእዮቶሙ ከመ ሳሕወ ደመና ዘኢይትገሰስ፡፡ ወመላእክተ ብርሃንኒ ይትመተሉ ወያስተርእዩ አምሳለ ሕፃናት እንዘ ኢኮኑ ሕፃናት ወያስተርእዩ በርእየተ አዕሩግ እንዘ ኢኮኑ አእሩግ፡፡ ወበከመ ከፈሎሙ ትእዛዘ እግዚአብሔር ያስተርእይዎ ለብእሲ ኀበ ተፈነዉ ወባሕቱሰ ማዕተበ ብርሃን ቦሙ እስመ መላእክተ ቅዱሳ እሙንቱ፡፡

፲፮ ወይቀንጽ ትፍሥሕት ውስተ ልቡ ለዘይሬእዮሙ እመሂ በራእይ ወእመሂ በሕልም፡፡ወመናፍስተ ስሕተትሰ ያደውዩ ለሰብእ ለእመ በጽሑ ጽላሎቶሙ ይደነግጽ ልበ ብእሲ እመ ርእዮሙ በራእይ አው በሕልም እስመ ተአምር ነፍስ ጸላኢሃ ወትፈርሆ እስመ መላእክተ ሙስና እሙንቱ፡፡ወሥጋሰ ንጽሕት እንተ ነሥአ እግዚእነ እምቅድስት ድንግል ሥጋ አበው ይእቲ ዘእምሥርወ አዳም ወአልቦቱ ተውላክ ለትሰብእተ መለኮት ዘእንበለ ጠባይዐ አዳም፡፡ወካዕበ አልቦ ተሕጻጸ እምጠባይዐ አዳም ዘእንበለ ፍና ኃጢአ ባሕቲቶን፡ ወብየ ግዱ ስምዕ ዘየዐቢ እምኵሉ ዘከመ አስተርአዮሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ እምድኅረ ተንሥአ እሙታን፡፡ ዕብ፩፥፲፬

፲፯ ይቤ ሉቃስ ወንጌላዊ ወእንዘ ዘንተ ይትናገሩ ቆመ ማእከሎሙ እግዚእ ኢየሱስ

ማቴዎስ የተናገረው እውነት ምስክርነት አለን አራት ሰዓት በሆነ ጊዜ በባሕር ላይ እየተራመደ ወደነርሱ መጣ ደቀመዛሙርቱ በባሕር ላይ ሲራመድ ባዩት ጊዜ ምትሐት ነው ብለው ደነገጡ ታወኩም መንፈስ የታያቸው መሰላቸው ግርማውንም ከመፍራት የተነሣ ጮሁ ያን ጊዜም ጌታ ኢየሱስ እመኑ አትፍሩ እኔ ነኝ ብሎ ተናገራቸው፡፡ ማቴ፲፬፥፳፫-፳፯

፲፭ የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ቢሆን ኖሮ ወንጌላዊ ምትሐት የታያቸው መሰላቸው ባላለ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ስለለበሰው ፍጹም ሥጋ የታያቸው መሰላቸው አለ፡፡ ለምን ምትሐት መሰላቸው የሌሊቱ ግርማ ያስፈራል የባሕርንም ሞገድ መርገጥ ለሰው ልጅ የተሰጠ አይደለምና በውኃ ላይ የሚመላለስ ሥጋ ባዩ ጊዜ ፈሩ፡ ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ አላወቁምና እኔ ነኝ አትፍሩ ባላቸው ጊዜ ግን አልፈሩም፡ ምትሐት ማለት የመናፍስት በልዩ ልዩ መልክ መታየት ነውና፡ ሥጋ የሌላቸው ሲሆኑ በሥጋ ለባሽ አምሳል ይታያሉ፡ አንድ ጊዜ ይታያሉ አንድ ጊዜ ደግሞ ይሠወራሉ መታየታቸውም እንደማይዳሰስ የደመና ተን ነው የብርሀን መላእክትም ሕፃናት ሳይሆኑ በሕፃናት አምሳል ሆነው ይታያሉ ሽማግሌዎች ሳይሆኑ በሽማግሌዎች አርአያ ይገለጣሉ፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዳላቸው በተላኩበት ሥፍራ ለሰው ይታዩታል፡ ዳሩ ግን የምስጋና መላእክት ናቸውና የብርሃን ማዕተብ አላቸው፡፡

፲፮ በራእይም ቢሆን በሕልምም ቢሆን ያያቸው ደስታ በልቡ ይዘላል፡ የስሕተት መናፍስት ግን ሰውን ጥላቸው ባረፈበት ጊዜ ያሳምሙታል በራእይ ወይም በሕልም ካያቸው የሰው ልብ ይደነግጣል ነፍስ ጠላቷን ታውቀዋለች ትፈራውማለች የጥፋት መላእክት ናቸውና ጌታችን ከቅድስት ድንግል የነሣት ንጽሕት ሥጋስ ከአዳም ባሕርይ የተገኘች የአባቶች ሥጋ ናት ከአዳም ባሕርይ በቀር የመለኮት ሰውነት ጭማሪ የለበትም ሁለተኛም ከኃጢአቶችም ወገን ብቻ በቀር ከአዳም ባሕርይ ጉድለት የለውም፡ ዳግመኛም ጌታ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ እንደታያቸው የሚናገር ከሁሉ የበለጠ ምስክር አለኝ፡፡ ዕብ፩፥፲፬

፲፯ ወንጌላዊ ሉቃስ ይህንንም ሲነጋገሩ ጌታ ኢየሱስ በመካከላቸው ቆም

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎሙ ሰላም ለክሙ ኢትፍርሁ ወኢትደን
ግፁ አነ ውእቱ፡፡ ወደንገፁ ወፈርሁ ወመሰ
ሎሙ ዘመንፈሰ ርእዩ፡፡ ወይቤሎሙ ምንት
ያደነግፀክሙ ወለምንትኑ ኀሊና የዐርግ ውስተ
ልብክሙ፡፡ርእዩ እደውየ ወእገርየ ከመ አነ
ውእቱ ወግሰሱኒ ወአእምሩ እስመ ለመንፈስ
ሥጋ ወዓፅም አልቦ ከመ ትሬእዩኒ ሊተ ወአነ
ብየ፡፡ወዘንተ ብሂሎ አርአዮሙ እደዊሁ ወእግ
ሪሁ፡፡ አጠንቅቅ አንብቦቶ ለዝ ቃል ከመ
ይትአመር ለከ ፍካሬሁ በተሊወ ንባቡ፡፡ይቤ
እግዚእ ለአርዳኢሁ እስመ ለመንፈስ ሥጋ
ወአጽም አልቦቱ ወአንሰ ብየ በከመ ትሬእዩኒ፡፡ዝ
ብሂል ኢይም ሰልክሙ ዘበምትሐት አስተርኢ ለክ
ሙ ወዘበመንፈሰ ጽላሎት እትናገረክሙ፡፡እስመ
ምትሐትሰ ያስተርኢ ወኢይትገሰስ እስመ ለመን
ፈስ አልቦቱ ሥጋ ወኢአጽም ግሱኒ ወአእምሩ እስ
መ ብየ ሥጋ ዘይትገሰስ ወአጽም ዘይትገሰስ፡፡
ወእምዝ አርአዮሙ እደዊሁ ወእገሪሁ ኀበ ተሰቅረ
በኃጸውንት መስቀል ወገቦሁ ኀበ ተርኀወ በኲናት
ሐራዊ፡፡ ሉቃ፳፬፥፴፱

፲፬ ተኀፈርኬ ኦ መንክዮስ ዘትቤ
ትስብእቶ ለክርስቶስ ምትሐት መድኃኒት፡፡
ናሁ ውእቱ ሰሊሁ አጽርዐ ሃየማኖትከ እንዘ
ይብል አንሰ ሥጋ ወአጽም ብየ፡፡ንሕነሰ ነአ
ምኖ ለክርስቶስ ከመ ፍጹም እግዚአብሔር
ዘከመ አቡሁ ወከመ ፍጹም እጓለ እመሕያው
ከማነ፡፡ወለነኒ ፍጽምት ሃይማኖትነ ወፍጽ
ምት ጥምቀትነ ወፍጽምት ቤተክርስቲያንነ፡፡

፲፭ ወበ እለ ይቤሉ ከመ እግዝእትነ
ማርያም ኢተወልደት በሩካቤ፡፡ እፎኬ ይብ
ልዋ ኢተወልደት በሩካቤ ዘለሊሃ አንከረት
ሶበ አብሰራ መልአክ እንዘ ይብል ወናሁ ትፀ
ንሲ ወትወልዲ ወልደ፡፡ወትቤሎ ድንግል
ለመልአክ እፎ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየ
አምር ብእሴ፡ሶበሰ እማ ፀንሰታ እንበለ ሩካቤ
እም ኢትቤ ድንግል እፎ ይከውነኒ ዝንቱ
እንዘ ኢየአምር ብእሴ፡፡ሰሚዐ ዜና ጽንስ
ዘኢልማድ አንከረት ወለተ ዳዊት፡፡ወእምዝ
ይቤላ መልአክ መንፈስቅዱስ ይመጽእ ላዕሌ
ኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ወዘኒ ይትወለድ
እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ
ልዑል፡፡ ወይእተ ጊዜ ትቤ ድንግል ነየ
አመት እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ
ወምስለ ብሂለ ዝ ቃል ኮና በከመ ይቤላ በአ
ኃይል ዘኢያስተርኢ ምስለ ቃለ ገብርኤል
እንተ መስኮት እዝና ወኀደረ ውስተ ማኅፀና
ዘኢለከፎ ርስሐት

ሰላም ለእናንተ ይሁን አትፍሩ አትደንግጡ እኔ
ነኝ አላቸው እነርሱ ግን ፈጽመው ፈሩ መንፈስ
የሚያዩም መሰላቸው፡ ምን ያስ ደነግጣችኋል
ስለምንስ አሳብ በልባችሁ ያድራል እኔ
እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ ዳሰሳችሁኝ
እወቁ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔ
ግን እንደምታዩኝ አለኝ አላቸው፡፡ ይህንንም
ተናግሮ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው አለ፡፡
ትርጉሙ እንዲረዳህ አገባቡን በመከተል ይህን
ቃል ለማንበብ ተጠንቀቅ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ
መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔ ግን
እንደምታዩኝ አለኝ አለ ይህ ማለት በምትሐት
ተገለጥሁላችሁ በመንፈስ ጥላም ተናገርኋችሁ
ማለት አይምሰላችሁ ምትሐት ይታያል ነገር
ግን አይዳሰስምና መንፈስ ሥጋና አጥንት
የለውምና ዳሰሳችሁኝ ዕወቁ እኔ የሚዳሰስ
ሥጋ የሚዳሰስም አጥንት አለኝና ከዚህ በኋላ
በመስቀል ችንካሮች የተቸነከረውን እጆቹንና
እግሮቹን በጭፍራም ጦር የተወጋውን ጐኑን
አሳያቸው፡፡ ሉቃ፳፬፥፴፱

፲፬ የክርስቶስ ሰውነቱ የአስማት ምትሐት
ነው ያልህ መንክዮስ ሆይ እፈር እነሆ እርሱ
ራሱ እኔ ሥጋና አጥንት አለኝ ብሎ እምነትህን
አፈረሰብህ እኛ ግን ክርስቶስን እንደ አባቱ
ፍጽም አምላክ እንደእኛም ፍጹም የሰው ልጅ
እነደሆነ እናምነዋለን ለእኛም ሃይማኖታችን
እንከን የሌላት ጥምቀታችንም እንከን የሌለባት
ቤተ ክርስቲያናችንም ሕጸጽ የማይገኝባት ናት፡፡

፲፭ እመቤታችን ማርያም በሩካቤ አልተ
ወለደችም የሚሉም አሉ እርሷ ራሷ መልአኩ
እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጂ
ያለሽ ብሎ የምስራች ሲነግራት መልአኩን
ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንደምን ይሆንልኛ
ል ብላ ያደነቀች እርሷን እንደምን በሩካቤ አልተ
ወለደችም ይሉአታል፡፡ እናቷ ያለ ሩካቤ ፀን
ሳት ቢሆን ኖሮ ድንግል ወንድ ሳላውቅ ይህ
እንደምን ይሆንልኛል ባላለች ነበር፡፡ የተለ
መደ ያይደለውን የጽንስ ዜና ሰምታ የዳዊት
ልጅ አደነቀች፡፡ ከዚህም በኋላ መልአኩ መንፈስ
ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኃይልም
ይጋርድሻል ካንቺም የሚወለደው ቅዱስ ነው
የልዑል ልጅም ይባላል አላት፡፡ ያን ጊዜም ድን
ግል የእግዚአብሔር ሴት አገልጋይ እነሆ እንዳ
ልከኝ ይሁንልኝ አለች፡፡ ይህን ቃል ከመናገር
ጋር እንዳላት ሆነላት፡የማይታይ ኃይል ከገብር
ኤል ቃል ጋር በጆሮዋ መስኮት ገብቶ የዚህ
ዓለም እድፍ ባላገኘው ማኅፀኗ አደረ፡፡ንጹህ
ቃል የሆነ የእግዚአብሔር ቃል በንጽህት ሥጋ

www.ethiopianorthodox.org

ዝ ዓለም፡፡ ቃለ እግዚአብሔር ቃል ንጹሕ ኀደረ ኀበ ንጽሕት ሥጋ፡፡እሳት ዘኢይትገሰሰ ተጠብለለ በአጽፈ ሥጋ ተሥዕለ ለሊሁ በማኅፀነ ሙላድ ወአልቦ መሥዕለ ዘይት ፈቀድ በእንቲአሁ እስመ ለሊሁ ውእቱ ሠዓሊ መላእክት በጠባይዓ እሳት ወነፋስ ወሠዓሊ እጓለ እመሕያው በጠባይዓ ሥጋ ወደም፡፡ በአይቴ እንከ እምከ ሀለት ድንግል ተሠግዎ እምእማ ዘእንበለ እምአቡሃ እስመ ኢኮነት ገባሪት ለእጓለ እመሕያው፡፡ውእቱሰ ገባሬሁ ለእጓለ እመሕያው አነመ ሥጋ ለርእሱ እማ ኅፀነ ድንግል ተኬነወ በከመ ፈቀደ ወአልቦ ዘይከልኦ ገቢረ ዘኀለየ በከመ ጽሑፍ ዘይብል ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሤይ ወየዐርግ ጽጌ እምጕንዱ፡፡ምንት ውእቱ ፀአተ በትር እም ሥርው ዘእንበለ ዘርአ ሙላድ ዘቅድስት ድን ግል እንተ ኮነት እምኀበ ኢያቄም ውስተ ማኅ ፀነ ሐና፡፡እስመ ዘርአ ዕሤይ ውእቱ ኢያቄም አቡሃ ለማርያም ወምንትኑመ ካዕበ ዕርገተ ጽጌ እምጕንዱ ዘእንበለ ሥጋዌ መለኮት እም ወለቱ፡፡ ሉቃ፩፥፴፫

፲፮ ስብሐት ለአብ ለዘፈነወ ወልዶ ውስተ ማኅፀነ ድንግል ከመ ትለዶ ዘእን በለ ሩካቤ፡ ወሰጊድ ለወልድ ለዘተወልደ እንበለ ሩካቤ እምእንተ ተወልደት በሩካቤ፡ አኰቴት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘቀደሳ ወአጽናዓ ከመ ትለ ድ በኢሩካቤ፡ሰላም ወሣህል ለቅድስት ቤት ክርስቲያን፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡ ወአሜን፡፡

፲፯ ተፈጸመ ዘለፉሁ ለመንክዮስ ዘሰመዮ ምትሐተ ለትስብእተ መድኅን፡ አጽ ሐፍከዎ አነ ጊዮርጊስ ምስኪን፡ ሱታፌ ሃይማ ኖቶሙ ለናዝራውያን፡ወልደ ትምህርቶሙ ለሐዋርያት ንጹሐን፡ለባሴ ጥምቀቶሙ ለመ ሀ ይናን፡ ገብር ፅቡስ እም ዐቀብተ አናቅጺሃ ለቤተክርስቲያን፡ ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዓ ለመ ዓለም አሜን፡፡ ወአሜን፡፡

ooooooooo /// oooooooo

አደረ የማይዳሰስ እሳት በሥጋ መጠቅለያ ተጠቀለለ፡ እርሱ ራሱ በመወለጃ ማኅፀን ተሣለ እርሱን ለመሣል የተፈለገ ሠዐሊ የለም፡ መላእክትን በእሳትና በነፋስ ባሕርይ የሣለ የሰውንም ልጅ በሥጋና በደም ባሕርይ የሣለ እርሱ ራሱ ነውና፡፡ እንግዲህ ከአባቷ ሳትወለድ ከእናቷ ብቻ ለመወለድ ድንግል በየት ተቻላት የሰውን ልጅ የፈጠረች አይደለችምና እርሱ ግን የሰው ልጅ ፈጣሪ ነውና፡፡ ከድንግል ማኅፀን ሥጋ ለራሱ ፈተለ፡ እንደወደደው ተጠበበበት፤ ከዕሤይ ሥር በትር ትወጣለች ከግንዷም አበባ ይወጣል የሚል እንደተጻፈ ያሰበውን ለማድረግ የሚከለክለው የለም፡ ከኢያቄም ተከፍላ በሐና ማኅፀን ከተፀነሰች ከቅድስት ድንግል የትውልድ ዘር በቀር የበትር ከሥሩ መወጣት ምንድር ነው፡፡ የማርያም አባቷ ኢያቄም ከዕሤይ ዘር ነውና ዳግመኛም ከመለኮት ከሴት ልጁ ሰው መሆን በቀር የአባባ ከግንዱ መውጣት ምንድር ነው፡፡ ሉቃ፩፥፴፫

፲፮ ያለሩካቤ ትወልደው ዘንድ ልጁን ወደ ድንግል ማኅፀን ለላከ ለአብ ምስጋና ይገባል፡ በሩካቤ ከተወለደችይቱ ያለሩካቤ ለተወለደ ለወልድም ስግደት ይገባል፡ ላከበራት ያለሩካቤም እንድትወልድ ላከበራትና ላጸናት ለመንፈስቅዱስም አኰቴት ይገባል፡ ሰላምና ይቅርታም ለቅድስት ቤተክርስቲያን ይሁን ለዘላለሙ አሜን አሜን፡፡

፲፯ የመድኅንን ሰውነት ምትሐት ያለው የመንክዮስ ተግሣጽ ተፈጸመ፡ ለእግዚአብሔር የተለየ የሃይማኖታቸው ተሳታፊ የንጹሀን የሐዋርያትም የትምህርታቸው ልጅ የምእ መናንንም ጥምቀት የለበስሁ የቤተክርስቲያንን ደጃፎች ከሚጠብቁት መካከል ደካማ አገልጋይ የሆንሁ እኔ ምስኪን ጊዮርጊስ አጻፍኋት ለእግ ዚአብሔር ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን፤ አሜን፡፡

ooooooooo /// oooooooo

www.ethiopianorthodox.org